የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

# ዜና ሠዕሐሊት

በሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ በየ2 ወሩ የሚወጣ የውስጥ ጋዜጣ

ቅጽ 1 ቁጥር 68 የካቲት 2017ዓ.ም

ርዕይ

በዓለምአቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ተቀባይነት ያለው የግብርና ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ ማየት፤

ተልዕኮ

የግብርና ቴክኖሎጂን፣ አገልግሎቶችን፤ ግብዓቶችና ምርቶችን ጥራት፣ ደህንነት፣ ፍቱንነት፣ፈዋሽነት፣ጤናማነትና ቀልጣፋነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል፤ መልካም ስም ያለውና፣ለአካባቢ ጥበቃ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ የቁጥጥር ተቋምና ስርዓት በመገንባትና የግብርና ቁጥጥር ስራዎችን በመተግበር፣ የሀገር ውስጥ እና የአለም ገበያ ተደራሽነትና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለላቀ ሀገራዊ ጥቅምና የኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቀትን አስተዋፅኦ ማበርከት

እሴቶች

- ታማኝነት
- ሚስጥር ጠባቂነት
- ቁርጠኝነት
- የህግ የበላይነት
- ተጠያቂነት
- ለደንበኛና ተገልጋይ ትኩረት
- አለማዳላት
- አጋርነት
- ግልጽነት።
- ምላሽ ሰጪነት

አድራሻ፡- ፖ.ሳ.ቁ 31303

ስልክ ቁጥር ፡- 0115534520

የውስጥ መስመር፡- 227/234

ዌብሳይት:- http:www.eaa.gov.et

ፌስቡክ:- Eaa Ethiopian Agricultural Authority

ቴሌግራም:-eaapr_1234

## የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን በኢ-ሰርቪስ ኦን ላይን ላይ 36 አገልግሎቶችን እየሰጠ መሆኑ ተገለፀ።







የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ሁሉም ስራዎች ላይ ወረቀት አልባ የሆነ ቴክኖሎጅን በመጠቀም እና የኢ- ሰርቪስ ኦንላይን አገልግሎቶችን በማበልፀግ ሰራተኞችን አስልጥኖ ወደ ስራ መግባቱ ተገለፀ።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ዲሪባ ኩማ በመክፈቻ ንግግራቸው ባለስልጣኑ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣትና በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የቁጥጥር ተቋም ለመፍጠር በተለይም ወረቀት አልባ የኢ-ሰርቪስ ኦንላይን ቴክኖሎጅን በመጠቀም ውስብስ መቀነስና በተለይም ተገልጋዮች ከጊዜ፣ ከገንዘብና ሌሎች ጫና ከሚያደርስባቸው የአሰራር ሂደቶች ወጥተው ግልፅ፣ፈጣንና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎቶችን እንዲገኙ እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል።

ባለስልጣኑ መ/ቤቱ ሁሉንም አገልግሎቶች በኢ-ሰርቪስ ኦንላይን አገልግሎት ለመስጠት እየሰራ ሲሆን 38 የሚሆኑ አገልግሎቶችን በኦንላይን ሰርቪስ እየሰጠ ይገኛል። በመሆኑም 27 የሚሆኑት በሂደት ላይ መሆናቸውን የገለፁት ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በፀደጉት አገልግሎቶች ላይ ባለሙያዎች

ወደ ገጽ 2 ዞራል!

ከገጽ 1 የዞረ..

በቂ ስልጠና አግኝተው ወደ ስራ መግባታቸውንም አያይዘው ተናግረዋል።

ከፔራን የመጡት ባለሙያ አቶ አቤል ተክላይ የኢ ሰርቪስ ኦላይን አገልግሎት የአጠቃቀም ሂደቱንና ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ በዘርፉ ላሉ ባለሙያዎች አጭር ገለፃ አድርገዋል።

በባለስልጣኑ የእንስሳት ዘርፍ ሪጉላቶሪ ም/ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሀሚድ ጀማል በበኩላቸው ሁሉም የአሰራር ስርዓቶች ዲታላይዜሽን ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ የአሰራር ስርዓታችንን ማዘመንና በቴክኖሎጂ የበለፀገ ተቋምን መገንባት ይኖርብናል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የዕፅዋት ዘርፍ ሪጉላቶሪ ም/ዋና ዳይሬክተር ክቡር አቶ ወንዳለ ሀብታሙ የኢ-ሰርቪስ ኦንላይን ቴክኖሎጅ ተግባራዊነት ከሌሎች ተቋማት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመገንባት፣ ከተገልጋዮች ጋር ያለውን የአሰራር ስርዓት ግልፅና ቀልጣፋ ለማድረግና ብልሹ አሰራሮችን ለማስቀረት እንዲሁም ተቋሙ በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ውጤታማ እንዲሆን የሚያግዝ ነው ብለዋል። ከገፅ 2 የዞረ

ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሁሉም ፋብሪካዎች የእንስሳት መኖ ግበዓት (ፈሩሽካን) ያመርታሉ ። በዚህ መሰረት ከአያያዝ (አቀማመጥ)፣ ከንፅህና አጠባበቅና ከቆይታ ጊዜ ጋር በተያያዘ ያለውን ሕግና መመሪያውን ጠብቀው ከመስራት አንፃር እንዲሁም ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ የእንስሳት መኖ ግበዓት(ጥሪ ዕቃ) ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲደርስ ለማድረግ ያለባቸውን ክፍተት በማሳየትና ለቀጣይ አስተካክለው እንዲሰሩ በተለይም የእንስሳትን ጤና መጠበቅ የህረተሰብን ጤና መጠበቅ መሆኑን እንዲረዱ ግንዛቤ በመፍጠር ከዚህ በተሻለ ሕግና መመሪያውን ተከትለው በአግባቡ እየሰሩ ያሉትን ደግሞ በማበረታታት ውጤታማ የሆነ የስራ ምልከታ፣ ክትትልና ድጋፍ ተካሂዷል።

**ህግና መመሪያውን ተከትሎ በመስራት የባለስልጣኑን የቁጥጥር ስራ ማሳለጥ እንደሚገባ ተገለፀ!!!**



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት፣ ምርትና አገልግሎትን ብቃት፣ ጥራት፣ ፍቱንነት፣ ጤንነት እና ደህንነት በማረጋገጥ አርሶና አርብቶ አደሩ እንዲሁም የሰፋፊ እርሻ ባለሃብት የላቀ ቴክኖሎጂ በስፋት እንዲጠቀም ማድረግ፣ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፤ ፍላጎት ተኮር የሆኑ ደረጃዎች እንዲወጡ በማድረግ የምግብና ሥነ ምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።

በመሆኑም በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የህግ አገለውግሎት ስራ አስፈፃሚ ባለስልጣኑ የተጣለበትን የስራ ሀላፊነት እንዲወጣ እና የቁጥጥር ስራው የተሳለጠና ተጨባጪነት ያለው እንዲሆን በባለስልጣኑ የስራ ሀላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት በሚያከናውኗቸው ስራዎች ላይ ህግና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰሩ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።

በዚህም መሰረት የባለስልጣኑ የህግ አገልጎሎት ስራ አስፈፃሚ ከእንስሳት መኖ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ጋር በመሆን አራት በተመረጡ ከተሞች ላይ ማለትም አዳማ፣ሞጆ፣ቢሾፍቱና ዱከም በመገኘት የእንስሳት መኖ ምርት ግበዓት ማምረት በተመለከተ ክትትልና ድጋፍ አድርገዋል።

በእነዚህ አራት ከተሞች በርካታ የእንስሳት መኖ ግብዓት አምራቾች ያሉ ሲሆን 30 በሚሆኑ ድርጅቶች ላይ

ወደ ገፅ 2 ዞሯል

PAGE 3

# በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭና ወደ አገር ውስጥ የገባ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ላይ ውጤታማ ስራ መከናወኑ ተገለፀ!!!



የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ከሚያከናውናቸው በርካታ የቁጥጥር ስራዎች ውስጥ አንዱ በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ላይ ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭ የሚላክና ወደ አገር ውስጥ የሚገባ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ላይ ሲሆን በ2017 ዓ.ም በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ስራ አፈፃፀም ላይ በርካታ ውጤታማ ስራዎች ተከናውነዋል።

በዚህም መሰረት በዚህ ግማሽ ዓመት 195000 ወደ ውጭ የሚላክ የቁም እንሰሳት/ዳልጋ ከብት፣ ግመል/ በግ፣ፍየል/ በኳራንትን ጣቢያዎች ውስጥ በማቆየት አስፈላጊውን ክትባትና የጤና ምርመራ በማድረግ ጥራቱና ጤንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 280000 የቁም እንሰሳት ጥራትና ጤንነቱን በማረጋገጥ ወደ ተቀባይ ሀገራት የተላከ ሲሆን አፈጻጸሙም 107% ሆኗል።

በተጨማሪም 272000 ወደ ውጭ የሚላክ የለማ እንቁላል ጤንነት እና ደህንነቱ በማረጋገጥ ወደ ውጭ ለመላክ ታቅዶ 3420000የለማ እንቁላይ በኳራንቲን ሰርትፊኬሽን በመስጠት እንዲወጣ የተረገ ሲሆን አፈጻጸሙም ከ100% በላይ መሆን ችሏል።

ሌላው ወደ ተቀባይ ሀገራት ለሚላኩ የማርና ሰም ምርት ላይ ድርጅቶች የኢንስፔክሽን እንዲሁም የላብራቶሪ ምርመራ ተደርጐላቸው 220 ቶን ማርና ሰም ለመላክ ታቅዶ 118 ቶን የጤና አገልግሎት ሰርትፊኬት በመስጠት እንዲላኩ የተደረገ ሲሆን ይህም አፈጻጸሙ 56% የሆነ ሲሆን አፈጻጸሙም ዝቅ ያለበት ምክንያት የሀገር ውስጥ ፍላጐት መጨመር እና የዋጋ ንረት መኖሩ ነው፡

በዚህ ስድስት ወር 1785450 ያለቀለት ቆዳና ሌጦ የቨተርነሪ ሳኒተሪ ሰተፍኬት ለመስጠት ታቅዶ 2913765 የሳኒተሪ ሰርትፊኬት በመስጠት ከሀገር እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም >100% ሆኗል። ሌላው ለ345000 ወደ ሀገር የሚገባ የአንድ ቀን ጫጩትና የለማ እንቁላል ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 251810 /73%ተከናውኗል።

እንዲሁም 138 ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባ የተሻሻለ ዳልጋ ከብት ጤንነቱ እና ደህንነቱ ለማረጋገጥ ታቅዶ 298 / ከ100% በላይ ተከናውኗል።

በዚህ ግማሽ ዓመት 6000 ወደ ዐገር ለሚገባ አባላዘር ጤንነቱ እና ደህንነቱ የማረጋገጥ ሥራ ለመስራት ታቅዶ 96955 ከ100% በላይ ተከናውኗል።

ወደ ገፅ 4 ዞሯል

**በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር ጥራቱና ጤንነቱ የተረጋገጠ ወደ ውጭና ወደ አገር ውስጥ የገባ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ላይ ውጤታማ ስራ መከናወኑ ተገለፀ!!!**

**ከገፅ 3 የቀጠለ**

በተጨማሪ በኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ቁጥጥር የተከናወኑ ሌሎች ክንውኖች
አዲስ የኳረንቲን ጣቢያ ግንባታ ሲሆን ይህም ከDRIVE project ጋር በመሆን በጥናት በተለዩ ሁለት ቦታዎች ላይ አዲስ የኳረንቲን ጣቢያ ግንባታ ለማከናወን በኦሮሚያ ክልል በረና ዞን ሞያሌ ወረዳ እና ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ቦርዴ ወረዳ የቦታ መረጣና ርክክብ ስራ ተከናውኗል።

ሌላው በየዓመቱ ወደ አውሮፓ ገበያ የሚላክ የማር ምርት ላይ የሚደረገው የማር ቅሪት ምርመራ በዚህ ግማሽ አመት ለ16ኛ ጊዜ ከUNIDO Project በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሀገር አቀፍ የማር ናሙና ማሰባሰብና ከሀገር ውጪ ጀርመን ሀገር ባለው የINTERTEK ለብራቶሪ የማስመርመር ስራ ተጣናቆ የአናሊሲስ ስራና ዶክመት ዝግጅት እየተከናወና ይገኛል።
ከዚህ ባለፈ 24000ኪ/ግ የተፈጨ ቀንድና 158 ኪ/ግ ዝባድ የጥራትና ደህንነት ምርመራ በማድረግ ከምንም የበሽታ ምንጭ የፀዳ መሆኑን በማረጋገጥ የሰኒተሪ ሰርትፊኬት በመስጠት ከሃገር እንዲወጣ ተደርጓል። እንዲሁም በአመቱ በእቅድ ባይያዝም 130 የተለያዩ ዱር እንስሳትን አካላት የጥራትና ደህንነት ምርመራ በማድረግ ከምንም የበሽታ ምንጭ የፀዳ መሆኑን በማረጋገጥ የሰኒተሪ ሰርትፊኬት በመስጠት ከሃገር እንዲወጣ ተደርጓል።

ሌላው 75 የዳክዬ ላባ  ካርቶን ለጃኬት መስርያ የሚሆን የመግቢያ ፍቃድ ተሰቶ እንዲገባ ተደርጓል። ለምርምር አገልግሎት በቀረቡት 224 የመኖ ናሙናዎች ላይ የጥራት ፍተሻ አግልግሎት መስጠት ተችሏል። በተጨማሪም ከላቦራቶሪ ምርመራ ሥራዎች የተረፉ የመድኃኒት ናሙናዎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት ከኦሮሚያ እንስሳት እና ዓሣ ሃብት ኤጀንሲ በተጠየቀው የድጋፍ ጥያቄ መሠረት በቦረና ዞን ለ6 ወረዳዎች በተወካያቸው በኩል በማስተላለፍና ጥቅም ላይ እንዲውል የማድረግ ስራ ተከናውኗል።

**የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል ተመራጭ የልኅቀት ማዕከልና ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያለው የጥራት ምርመራ ላብራቶሪ ሆኖ እየሰራ ይገኛል::**

**ዶ/ር ናርዶስ ተፈራ የማይክሮባዮኦሎጅ ላብራቶሪ መሪ ስራ አስፈፃሚ**



የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል ሰኔ 2006 ዓ/ም የተቋቋመ ሲሆን  ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ነው:: ዋና  ዓላማው ቁጥጥር የሚደረግባቸው ምርቶችን ጥራት ተስማሚነት በላቦራቶሪ ፍተሻ ሥራ በማረጋገጥ የእንስሳት እና የህብረተሰብ ጤና አገልግሎት ማሻሻል ነው። በመጀመሪያዎቹ ጥቂት አመታት በርካታ ሥራዎች በመፈጸም ተቋሙን በሰው ኃይል እና አስፈላጊ የላቦራቶሪ ግብአቶች እንዲሟላ ከተደረገ በኃላ በ2009 ዓ/ም መጨረሻ አከባቢ በተመረጡ የእንስሳት መድኃኒት ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት መስጠት ጀመረ። በዚህ መሰረት በአሁኑ ወቅት ላብራቶሪው ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራትና ደህንነት የላብራቶሪ ምርመራ አገልግሎት በመስጠት የእንስሳት ጤና፣ ምርታማነትና የገበያ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ተመራጭ የልኅቀት ማዕከልና ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያለው የጥራት ምርመራ ላብራቶሪ ሆኖ እየሰራ ይገኛል::

**ወደ ገፅ 5 ዞሯል**

ይህ የእንስሳት ምርትና ግብዓት ጥራት ምርመራ ማዕከል ከሚሰራቸው በርካታ ስራዎች አንዱ የማይክሮባዮኦሎጅ ላብራቶሪ ምርመራ ነው። በዚህ ዘርፍ መሪ ስራ አስፈፃሚ ሆነው የሚሰሩት ዶ/ር ናርዶስ ተፈራ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን በዝርዝር እንደሚከተለው አብራርተውልናል።

የማይክሮ ባይኦሎጅ ላብራቶሪ 3 ላብራቶሪዎች ያሉት ሲሆን አንደኛ፡- የእንስሳት መድሀኒት ጥራትና ምርመራ ብቃት ዴስክ እና ሁለተኛው የእንስሳት ክትባትና ሆርሞን ተያያዥነት ባዮሎጅካሎች ጥራት ምርመራ ዴስክ እንዲሁም ሶስተኛው የእንስሳት ምርትና መኖ የማይክሮባዮሎጅካል ጥራትና ደህንነት ምርመራ ላብራቶሪ ዴስክ ይባላሉ።

እነዚህ ላብራቶሪዎች የየራሳቸው የሆነ የምርመራ ላቦች ያሏቸው ሲሆን በመሳሪያና በሰው ሀይል የተደራጁና ራሳቸውን የቻሉ የምርመራ ላብራቶሪዎች ናቸው። እነዚህ ላብራቶሪዎች በዋነኛነት የሚሰሩት ለምሳሌ አንደኛው የእንስሳት መድሀኒት ጥራትና ምርመራ ብቃት ብናይ አራት መሰረታዊ የምርመራ ስራዎችን ይሰራል። የመጀመሪያው የእንስሳት መድሀኒት ጥራት ደህንነት ምርምራ ላብራቶሪ በካይ ተህዋሲያን መጠን በስታንዳርዱ መሰረት መሆኑንና አለመሆኑን ያረጋግጣል፣ ኢንዶቶክሲን ምርመራ ያደርጋል፣ ከዚያ ባለፈ ደግሞ አንድ መድሀኒት የማዳን አቅሙ ምን ያህል ነው የሚለውን ይሰራል። ሌላው ዋናው ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ በአለማችን ስጋት የሆነውን አንቲማይክሮሬሲስታንስ ሰርቪላንስ ፕሮግራም የሚመራና የሚያስተባብር የምርመራ ክፍል ነው።

ይህ የምርመራ ላብራቶሪ ክፍል መቋቋሙና እነዚህን የምርመራ ሂደቶች ማከናወኑ የሚሰጠው ጥቅም አንደኛ ለባለስልጣን መስሪያቤታችን የእንስሳት መድሀኒትን ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ሊሆን ይችላል በአገር ውስጥ የሚመረቱትን ገበያ ላይ ሆነው ለተጠቃሚው ወይም ደግሞ ለአርሶ አደሩ ከመሰራጨቱና አገልግሎት ከመዋሉ በፊት በምርመራ ላይ የተመሰረተ ወይም የተረጋገጠ የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ ነው። ጥራታቸው ባይረጋገጥ ወይም ደግሞ እነዚህ መድሀኒቶች ስቴሪያል መሆን እያለባቸው እስቴሪያል ባይሆኑ የበካይ ተህዋሲያን መጠናቸው ከሚፈለገው የጥራት ወይም የብክለት መጠን በላይ ሆኖ ቢገኝ እንደ ቶክሲን ቢኖር ወይም ፈዋሽነታቸው ያልተረጋገጠ ቢሆን ምን ሊያስከትሉ ይችላሉ ብንል አንደኛ ፈዋሽ ላይሆኑ ይችላሉ ሁለተኛ የጎንዮሽ ጉዳት ሊኖራቸው ይችላል። ምክንያቱም እንስሳውን ለማከም ብለን የምንሰጠው መድሀኒት ጉዳት ሊያደርስበት ይችላል። ለምሳሌ ከኢንዶቶክሲን እና ከበካይ ተህዋሲያን ነፃ ካልሆነ ለእንስሳቱ በማዳን ፈንታ ሌላ በሽታ ልንሰጠው እንችላለን ይህ ደግሞ ምርትና ምርታማነትን በመቀነስ በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያደርሳል ። አብዛኛው ሳይንስ እንዳረጋገጠው ከ65-75 % የሚሆነው በሽታ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፍ ሲሆን ከእንስሳት ወደ ሰው ሊተላለፉ የሚችሉ በሽታዎችን ማከምና ማስቀረት እየቻልን ሳይታከሙ ቀርተው በምግብ አማካኝነት በአብዛኛው የምንመገባቸው ሊሆኑ ይችላሉ ከዚያ ባለፈ እንደ ውሻ ድመት ያሉትን ደግሞ የቤት እንስሳት ብለን የምንይዛቸው ሊሆኑ ይችላሉ እነዚህ ጤንነታቸው

**ወደ ገፅ 6 ዞሯል**

**ከ ገፅ 5 የዞረ**

ካልተጠበቀ ዞሮ ለማህበረሰቡና ለሚንከባከባቸው ሰው የጤና ተፅዕኖ ያሳድራሉ ማለት ነው። ይህንን ለመከላከል ጥራቱና ደህንነቱ ተረጋግጦ ወደ ገበያ እንዲደርስ የእንስሳት መድሀኒት ማክሮባዮሎጅካል ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው።

ሁለተኛው ላብራቶሪ የክትባት ጥራት ምርመራ ላብራቶሪ ሲሆን ይህ ላብራቶሪ በአገር ውስጥ የሚመረቱ ክትባቶችንና ከውጪ የሚገቡ ክትባቶችን በመስፈርቱ መሰረት ጥራትና ፈዋሽነቱን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል። በዚህም መሰረት በእንስሳት ጤና ላይ እና በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በመቀነስ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ጉልህ አስተዋፆ አለው። በተጨማሪም እንስሳቶችን ከበሽታ መከላከል ብቻ ሳይሆን እንስሳቶችን ለማሳከም ከሚወጣው የጊዜና የገንዘብ ብክነትን ይከላከላል እንዲሁም መድሀኒት በመውሰድ ሊመጣ የሚችለውን የመድሀኒት መላመድ በሽታን ይቀንሳል።

ሌላው በሶስተኛ ደረጃ የሚገኘው የመኖ ማይክሮ ባዮሎጅካል ጥራትና ደህንነት ምርመራ ሲሆን ዋና ተግባሩ የእንስሳትን ጤንነት ማሻሻል ነው። ይህም ሲባል ጥራቱን የጠበቀ ምግብና ክትባት እንዲያገኙ በማድረግ ጤናማ የአረባብ ስርዓት እንዲፈጠር ማድረግ ነው። ጤናማ የአረባብ ስርዓት ሲባል የሚውሉበትንና የሚያድሩበትን ምቹ ከማድረግ ባለፈ ለምግብነት የምንሰጣቸውን መኖና ውሃ ደህንነታቸውና ጥራታቸው የተረጋገጠ እንዲሆን ማድረግ ነው።

ሌላው የዛሬው መኖ የነገ ምግብ በመሆኑ እንስሳቶች የሚመገቡትን መኖና የሚጠጡትን ውሃ ጤንነቱንና ደህንነቱን ካላረጋገጥን የሰው ልጅ ነገ በሚመገባቸው የእንስሳት ተዋዕፆዎች ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ። በዚህም መሰረት በአለም አቀፍ ደረጃ በተደረገው ጥናት መሰረት ከእንስሳት ምርት ጋር በተያያዘ ስጋ፣ ወተትና እንቁላል ላይ አንድ የጤና ድርጅት ባወጣው ሪፖርት ከዛሬ 10 እና 15 ዓመት በሳይንስ የተገመተው በየአመቱ ቢያንስ ከ10 አንድ ሰው ወይም 600 ሚለየን ህዝብ ከምግብ ጋር በተያያዘ ይታመማል፤ እንዲሁም ከምግብ መበከልና መበረዝ ጋር ታያይዞ ደግሞ 400 ሽህ ሰዎች በየዓመቱ ይሞታሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ 110 ቢሊየን ዶላር በየዓመቱ እንከስራለን ማለት ነው። ይህ ኪሳራ የሚታየው ከአደጉት አገሮች ሳይሆን ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ውስጥ ሲሆን ከዚህም ውስጥ አንዷ ኢትዮጵያ ናት ይህ በሽታ በብዛት የሚያጠቃው ደግሞ 40% ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህፃናቶች መሆናቸው ተገልጿል። ይህ ደግሞ ነገ አገር ተረካቢ የሆኑትንና በተለይም የበሽታ መከላከል አቅማቸው ያልጎለመሰ እድገታቸውን ያልጨረሱ ህፃናትን በአብዛኛው ያጠቃል ማለት ነው። በተጨማሪም በዓለም ላይ 125 ሽህ የሚሆኑት ህፃናት ከምግብ ጋር በተያያዘ ይሞታሉ። ወደ እኛ አገር ስናመጣው በትክክል ዳታዎች ቢሰሩ ያለው የማህበረሰቡ ኑሮ ምን ይመስላል ምን ያህሉ ጥራቱ የተረጋገጠ ወተት፣ ስጋና እንቁላል ያገናል የሚለው ቢጠና ጉዳቱ ከዚህ የከፋ ሊሆን ይችላል ማለት ነው።

ይህ ጥናት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተጠና እውነታ ነው።

**ወደ ገፅ 7 ዞሯል**

ከገፅ 6 የዞረ

ይህ ችግር በአገራችን ሊባባስ የቻለው ያለው የቁጥጥር ስርዓት ደካማ መሆኑ ነው፡፡ ከ3 ዓመት ወዲህ የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን እንደ አዲስ መቋቋሙ ያለውን ችግር ሊቀርፍ የሚችል ተቋም በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡

ሌላው አገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካ 1ኛ በዓለም አቀፍ ደረጃ 10ኛ የእንስሳት ቁጥር ያላት አገር ስትሆን እስካሁን ባለው ሆኔታ ምንም እንኳ ከሌሎች አገሮች በተሻለ በእንስሳት ሀብት የበለፀገች አገር ብትሆንም ጥራቱን የጠበቀና ተወዳዳሪ ምርት እስካልተመረተ ድረስ ወደ ኋላ መቅረቷ እሙን ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ችግር ሊቀርፍ የሚችልና በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያገኘ የእንስሳት መኖ ጥራት ደህንነት ምርመራ ላብራቶሪ መኖሩ ለቀጣይ ስራ ትልቅ አስተዋፆ አለው፡፡

ስለሆነው ላብራቶሪው በማክሮባዮኦሎጅ ላብራቶሪ ዘርፍ ከላይ ባየናቸው 6 የምርመራ አይነቶች ላይ ዕውቅና አግኝቷል፡፡ ይህም የአገራችን ዜጋ ጥራቱን የጠበቀ ምርት ስለማግኘቱ የምናረጋግጥበት አቅም አለን ፡፡ እንዲሁም ወደ ውጪ የሚላኩ የእንስሳት ምርት ስጋ ፣ ወተት ፣ማር ሊሆን ይችላል ጤንነታቸውና ደህንነታቸው ይረጋገጥልኝ የሚል አካል ቢኖር ሊያረጋግጥ የሚችል የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የእንስሳት ግብዓት ምርት ጥራት ምርመራ ማዕከል መፍጠርና ማቋቋም ችለናል ማለት ነው፡፡

PAGE 7

## የተሻለ የግብርና ምርት ለማግኘት የቁጥጥር ስራው መጠናከር እንዳለበት ተገለፀ፡፡







በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የህግ ስራ አስፈፃሚ የባለስልጣኑን የቁጥጥር ስራ ለማጠናከርና ውጤታማ የግብርና ምርት እንዲኖር በዘርፉ ከተሰማሩ ባለሙያዎች ጋር ተቀናጅቶ ለባለድርሻ አካላት ህግና መመሪያዎችን አንዲሁም አዋጅና ደንቦችን ተከትለው እንዲሰሩ ግንዛቤን ይፈጥራል፡፡

በዚህ መሰረት የባለስልጣኑ የህግ ጉዳዮች ስራ አስፈፃሚ በደቡብ ክልል ከሚገኙ ዓቃብያን ህግ ፣ የዕፅዋትና የዘር እና የእንስሳት መድሀኒት፣እንዲሁም የፀረ ተባይ ማዳበሪያ ባለሙዎችና ፖሊሶች በተገኙበት ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና አካሄደ፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን (በአዋጅ 1263/2013 እና በደንብ ቁጥር 509/2014) መሰረት በግብርና ዘርፉ የተጠናከረ የሬጉላቶሪ ሥርዓት በመዘርጋት እና

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

ከገፅ 7 የዞረ

በመተግበር በዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን እያሳደገ ይገኛል ያሉት የባለስልጣኑ የህግ ባለሙያ አቶ ሞገስ ብርሀኑ በተለይም ይህን ዓላማ ለማሳካትና እንዲሁም በሰው፣በእንስሳት፣ በአካባቢእና በእፅዋት ጤና የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስና መመሪውን የተከተለ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት ግንዛቤን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

የባለስልጣኑ የህግ ባለሙያ የሆኑት አምሳለ ተፈራ በበኩላቸው የስልጠናው ዋና ዓላማ በተለይም በአምራቾችና በገዥዎች ላይ ያለውን የግንዛቤ እጥረት በመፍታት ህግና መመሪውን አውቀው እንዲሰሩና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ህገወጥ አሰራርን መቀነስ ነው ብለዋል፡፡ ስልጠናው ተሳታፊዎችም የግንዛቤ ፈጠራ ስራው ወሳኝና ውጤታማ መሆኑን ገልፀው በተለይም በቅንጅት በመስራት የሚታዩ የአስራር ክፍተቶችን በመለየት ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻም ባለሙያዎቹ የህግ ጥሰቶችን ለመከላልና የቁጥጥር ስርዓቱን ለማጠናከር ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ ፈጠራ እንደሚያስፈልግና በተቀናጀ የባለድርሻ አካላት ጥምረት አማካኝነት ሕገ-ወጥ የግብርና ግብዓት ፤ የግብርና ምርት እና የግብርና ቴክኖሎጂ ንግድና ዝውውርን መቆጣጠር እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡ **ከቀጣዩ ገፅ የቀጠለ**

በመጨረሻም የባለሥልጣኑ የፅ/ቤት ኃላፊ አቶ መሰሉ ዋጋው የቀረበው ተሞክሮ በጥንካሬ እንድንጓዝና መብትና ግዴታችን ተጠቅመን ውጤት እንድናመጣ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘው የባለሥልጣኑ የስራ አመራር መሪ ስራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ አበበ ገለታ በበኩላቸው ሴቶች በሁሉም አገራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ የላቀ ነው በማለት እንደ ባለስልጣን መ/ቤት የሪጉላቶሪ ስራው ውጤታማ እንዲሆን ሴቶች ጉልህ ሚና እንዳላቸው ገልፀው ለቀጣይ ስራችንም በጥንካሬና በቅንጅት ወደ ፊት መጓዝ እንዳለብን አሳስበዋል፡፡

## በሴቶች ተሳትፎ ሁለንተናዊ እድገት ይረጋገጣል!!!

በኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን የሴቶች ቀን በአለም አቀፍ ደረጃ 114ኛ ጊዜ በአገራችን ደግሞ ለ 49ኛ ጊዜ" ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ሁሉን አቀፍ ለውጥ በሴቶች ተሳትፎ ይረጋገጣል" በሚል መሪ ቃል ተከበረ ።

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አምባሳደር ድሪባ ኩማ በሴቶች ቀን ተገኝተው ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ ሴቶች በብዙ ትግሎች ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉና ትልቅ ድል ያስመዘገቡ መሆናቸውን ገልፀው በተለይም ባለስጣኑ በሚሰራው የቁጥጥር ስራ ላይ የተጠናከረና በአለም አቀፋ ደረጃ ተቀባይና እውቅና ያለው ተቋም ሆኖ እንዲሰራ የሴቶች ተሳትፎ ትልቅ ሚና አለው ብለዋል፡፡

የሴቶችና ማህበራዊ አካቶ ትግበራ ስራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድማገኝ የሴቶችን ቀን ስናከብር ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊይና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን በተለይ ሴቶች መብትና ግዴታቸውን በመጠቀም በማህበረሰቡ የሚደርስባቸውን ኋላቀር አስተሳሰብ በመታገል ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንዲችሉ አስተማሪና አረዕያ የሆኑ የታላላቅ ሴቶችን ተሞክሮም አቅርበዋል፡፡

የባለሥልጣኑ የእንስሳት መድሀኒት ሪጉላቶሪ ምዝገባ ፈቃድ ዴስክ ኃላፊ ወ/ሪት ሰገዱ ሽፈራው በበኩላቸው በስራ ህይዎታቸው ያሳለፉትን ተሞክሮ ያቀረቡ ሲሆን አያይዘውም ከራሳቸው ተሞክሮ ተነስተው ሴቶች በተሰማሩበት ስራ ላይ የትኛውም ችግር ቢገጥማቸው የይቻላል መንፈስ በመያዝ ለቆሙለት ኣላማ በመታገል ውጤታማ እንዲሆኑ አስረድተዋል፡፡

ወደ ቀጣዩ ገፅ ዞሯል

# በፊ ሊሃሠ ደፎ

### የአለማችን አስገራሚ እውነታዎች

በሰማይ ላይ ቀስተ ደመናን መመልከት የተለመደ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በወንዝ ውስጥ ይህን ማግኘት እንግዳ ነገር ነው፡፡



“የአምስት ቀለማት ወንዝ” በመባል የሚታወቀው የካኖ ክሪስታሌስ ወንዝ በሰማይ ላይ ካለ ማንኛውም ቀስተ ደመና የበለጠ ደማቅ ነው ቀስተ ደመና አለው ይባልለታል።ይህ አስደናቂ ወንዝ በኮሎምቢያ ሴራኒያ ዴላ ማካሬና ብሔራዊ የተፈጥሮ ፓርክ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ወንዙ በቢጫ፣ በሰማያዊ፣ በአረንጓዴ እና በቀይ የሚያብብ ሲሆን ከግንቦት እስከ ህዳር ባለው ጊዜ ውስጥ ደግሞ ውበቱ ደምቆ ይወጣል፡፡ውሃው ጥልቀት በሌለው በዚህ ጊዜ ውስጥ የበለጠ ደማቅ ቀለሞችን ይመለከታሉ፡፡




### የታላላቅ ሰዎች አባባል

❖ዓለማችን በጣም እየተጎዳች ያለችው ከመጥፎ ሰዎች ክፋት ሳይሆን ከጥሩ ሰዎች ዝምታ ነው # ናፖሊዮን
❖በሕይወቴ አይሆንም ያሉኝን ሰዎች ሁላ ላመሰግን እወዳለሁ ምክንያቱም እነሱ እምቢ ስላሉኝ እኔ እራሴ ሄጄ አደረኩት #አንስታይን
❖በፈገግታ የተሞላ ፊት ችግር የለበትም ማለት አይደለም። ችግራቸውን የሚወጡበት መንገድ አላቸው እንጂ #ሼክስፒር
❖በብርሃን ስትሆን ሁሉ ነገር ይከተልሃል:: ጨለማ ውስጥ ከሆንክ ግን ጥላህ እንኳን አይከተልህም #ሂትለር
❖ሳንቲም ብዙ ድምፅ ያሰማል። ገንዘብ ግን ምንም አያሰማም። ስለዚህ ዋጋህ ሲጨምር ወሬህን እየቀነስክና! #ሼክስፒር
❖ታላቁ ጦርነት ራስን ማሸነፍ ነው። #ሼክስፒር

### አራዳው ተከሳሽ የፍርድ ቤት ውሎ

ወጣቱ በስርቆት ወንጀል ተከሶ ፍርድ ቤት ቀረበ፤የአንዲት ተማሪ የወርቅ የአንገት ሐብል ቀምተሀል። በሚል ክሱ ተደመጠ ምስክሮችም ቃላቸውን ሰጡ። ወጣቱም ስለ ተከሰሰበት ቃሉን እንዲሰጥ ተጠየቀ። የእምነት ክህደት ቃሉንም እንዲህ ሲል ሰጠ፡-በአንድ ወቅት ቺኬ ነበረች ልከርካት ትምሮ ቤት መረሸኩኝ እዚያም ደርሼ ጠየኳት እናም ጀለሳሞች እንሁን አልኳት እሷ ግን እንቢ ብላ ገጀረች እኔም ነቀልኩ። ምክንያቱም ከእሷ ፎንቃ እንደጠለፈኝ እያወቀች እንቢ ማለቷ ደንፋ አስያዘኝ። በጨማ ጥፊ አንዴ ልቀዳት ስል መቃዋ ላይ ያለውን ጩባዋን በአይኑካዎቼ ክልም አደረኩት። በቃ ያኔ ተከየፍኩበት። በውበቱ በጣም ስለፎነቀቁበት ከምመታት ብዬ መንጩ አርጌ ልመርሽ ስል ዛፓ መጥቶ ጋማ ብሎኝ ሸቤ ቤት ወረወረኝ ድርጊቱን ፎይጄዋለሁ። እናም ፍርድ ቤቱ መቼም የፎንቃን ሙድ ያውቀዋልና የጀለሴን ጩባ መንጩ እስከማደርግ ያደረሰኝ ፎንቃ መሆኑን ነቄ ብሎ አስተያየት እንዲያደርግልኝ አስክ አደርጋለው፡፡ አለ ወጣቱም ይህን ቃሉን ሰጥቶ እንደ ጨረሰ ዳኛው ግራ በመጋባት ስሜት የሚከተለውን ውሳኔ አስተላለፉ፡-የተከሳሽ ሙሉ ቃል በአማርኛ ተተርጉሞ በሚቀጥለው ቀጠሮ ይቅረብ እስከዛ ወጣቱ በእስር ቤት ይቆይ አለ።